ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

የኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎች አስቸኳይ የድረሱልን ድምፅ

‹‹. . . በዓለም ሊረዳን የሚችል አካል አለን? . . .እባካችሁን በተፈጠርንበት ምድራችን እየደረሰብን ካለው መከራ ታደጉን። አሁኑኑ!!››

ይህ የኦሞ ሸለቆ አካባቢ ነዋሪዎች የተማጽኖ ድምጽ ነው። ዛሬ በኦሞ ሸለቆ በሚኖሩ ዜጎቻችን ላይ በጠመንጃ ኃይል እየተፈፀመ ያለው ድርጊት አጅግ አሳሳቢና የመላውን ሰላም ወዳድና ፍትህ ናፋቂ ኢትዮጵያዊያንና ለሰብዓዊነት ቅድሚያ ለሚሰጡ ወገኖችን ሁሉ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ያምናል።

በኦሞ ሸለቆ የሚኖሩ ወገኖቻችን፣ የአስቸኳይ ድረሱልን ድምጻቸውን እያስተጋቡ ያሉት የህወሃት/ኢህአዴግ ጦር እያደረሰባቸው ያለው አረመኔነት የተሞላበት ግፍ፣ ሰብዓዊ መብታቸውን በመርገጥ እየፈፀመባቸው ባለው መከራ ሳቢያ ነው። እነዚህ ዜጎች በአገዛዙ ባለስልጣናት ትዕዛዝ አስቀድሞ መኖሪያቸው ዘንድ በተሰማሩ ወታደሮች አማካይነት ያለ አንዳች ማስጠንቀቂያና ምክክር መሬታቸውን በመንጠቅ በዶዘርና በከባድ ተሽከርካሪዎች የማፈናቀል አስነዋሪ ተግባር ተፈጽሞባቸዋል፡፡የቦዲ ብሄረሰብ አባላት በጭነት መኪና ቀያቸውን ለቀው ከተጋዙ በኋላ በመሬታቸው ላይ ስላላቸው መብት መንግስት እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም ምላሽ አላገኙም።

የጋራ ንቅናቄያችን በደረሰው መረጃ መሠረት ባለፈው ቅዳሜ ታህሳስ 28፣ 2004ዓም ምሽት ላይ ወ/ሮ ቢኮሉ የተባሉ ሴት ወደ ከብቶቻቸው እየተጓዙ ባለበት ወቅት በከባድ ጭነት መኪና ተገጭተው ይሞታሉ፡፡ የቀብር ስነሥርዓታቸው ከተከናወነ በኋላ ቤተሰቦቻቸው ሁኔታው እንዲጣራና አስፈላጊም የሆነው ካሣ ከፍትሕ ጋር እንዲሠጣቸው ቢጠይቁም ከመንግሥት የተሰጣቸው ምላሽ ማስፈራራትና ዛቻ ነበር፡፡ እንዲያውም የአካባቢው የመንግሥት ተወካይ የሟች ባለቤት እጃቸውን ለመንግሥት መስጠት እንዳለባቸውና እየፈጠሩ ላለው ችግር ወደ እስር ቤት መወሰድ እንዳለባቸው ያስታውቃሉ፡፡ ግለሰቡ በፈቃዳቸው እጃቸውን የማይሰጡ ከሆነ ‹‹እሳቱን ወደ እነርሱ›› እንደሚያመጡት ባለሥልጣኑ በእብሪት ተናግረዋል፡፡

እነዚህ ወገኖቻችን የሚደርስባቸው በደል እየተባበሰና ውጥረቱ እያየለ በመሄዱ የተቃውሞ ድምጻቸውን ቢያሰሙም ምላሹ በኦጋዴን፣ በጋምቤላና በሌሎች አካባቢዎች እንደተደረገው አስቀድመው በአካባቢው እንዲሰማራ በተደረገ ጦር ሠራዊት በመሳሪያ ሃይል በማስፈራራት፣ በማስገደድ ግልገል ጊቤ ቁጥር 3 ፕሮጀክት ዙሪያ ካለው ለም መሬታቸው እንዲፈናቀሉ ተደርጓል፣ አሁንም እየተደረገ ነው። ኤሌክትሪክ ለማመንጨት በሚል የግድብ ግንባታ ቢካሄድም አብዛኛው ውሃ የሚውለው ጥቂት የህወሃት ቁንጮዎችን ለመጥቀም ለተደራጀው የሸንኮራ እርሻ ነው። ከዚህ ፕሮጀክት ያካባቢው ነዋሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ የማይታሰብ ሲሆን በአንጻሩ የተፈጥሮን ስርዓት፣ የብዝሃ ህይወትና የአካባቢውን የአየር ንብረት ከኦሞ ሸለቆ ጀምሮ እስከ ኬንያ አደጋ ላይ እንደሚጥል መገመት የሚያዳግት አይሆንም፡፡

በኦሞ ሸለቆ ውስጥ የሚኖሩ ከ500ሺህ በላይ ነዋሪዎች አገሪቱን እየመራ ባለው ህወሃት/ኢህአዴግና በቀደምት አገዛዞች የተገፉና የተናቁ ኢትዮጵያውያን ናቸው። **የቦዲ፣ የሙርሲ፣ የኩዋጎ፣ የሱሪ፣ የሃመር፣ ካሮና ሌሎች ተመሳሳይ ህዝቦች በኢትዮጵያ ዋጋ ያላቸው ለቱሪዝም ገበያ ብቻ እንደሆነ በሁላችንም ዘንድ የታመነና የምናውቀው ነው።** ለዘመናት ሳይቀየር አብሯቸው ያለውን ኋላ ቀር አኗኗራቸውና ልማዳቸውን ለቱሪዝም ገበያ እያዋለ ያለው ህወሃት/ኢህአዴግ፣ አሁን ደግሞ መሬታቸውን ከመንጠቅ አልፎ ጦር ሠራዊቱን አሰማርቶ ኢሰብዓዊ ተግባር መፈጸሙን ተያይዞታል፡፡ ይህ ረገጣና ግድያ እስከመቼ በዚህ መልኩ ይቀጥላል?

በውጪ አገር በሚሊዮን ከሚቆጠሩት ኢትዮጵያውያን መካከል ከዚሁ ኦሞ አካባቢ በውጪ የሚገኘው አንድ ወይም ሁለት ሰው ብቻ እንደሆነ አንዳንድ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም የአካባቢውን ኋላቀርነትና የሕዝቡን በደል ከማሳየት አልፎ ምን ያህል የተረሱ ህዝቦች እንደሆኑም የሚጠቁም ነው፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩት በአገር ውስጥና በውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን የሚያስቡት ከእነዚህ ህዝቦች ይልቅ አንድ የኦሞ ወንዝ እንደሚበልጥ ነው። ይህም የመገፋታቸው ሌላኛው ገጽታ ነው። በተዛባ የፌደራል ስርዓት ውስጥ ያሉት የኦሞ ሽለቆ ህዝቦች፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ ትምህርት፣ የጤናና የተዛማጅ አገልግሎቶችን ከማንም በላይ ማግኘት ሲገባቸው፣ በተቃራኒው ውድ የሆነውን ሃብታቸውን፣ የተፈጠሩበትን ምድርና ውሃቸውን ተነጥቀዋል። ታዲያ ለነዚህ ህዝቦች ማን ጩኸታቸውን ይጩህላቸው? ማንስ ይናገርላቸው? ህወሃት/ኢህአዴግ ያሰማራቸው ወታደሮች ተቃውሞ ባሰሙት ላይ ማስፈራራት፣ ሰብአዊ መብታቸውን በመግፈፍና የሃይል ርምጃ በመውሰድ በስውር እየገደላቸው ይገኛል። ብሎም ሊያጠፋቸው ያስባል። ዓለምም ትኩረት ነፍጓቸዋል! እኛ ኢትዮጵያውያንስ?

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ በእነዚህ ውድ ዜጎቻችን ላይ የሚካሄደው ህግና ስርዓት የለቀቀ የመሬት ነጠቃና የመብት ረገጣ አሁን ደግሞ ግድያ ባስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲቆም ያስታውቃል፡፡ይህንን እየተባባሰና ሥር እየሰደደ የመጣ ችግር የምትገነዘቡ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከኦሞ ሽለቆ ህዝቦች ጎን በመቆም የተቃውሞ ድምጽ እንድታሰሙ ጥሪ እናስተላልፋለን።

የኦሞ ሽለቆ ህዝቦች አካላችን ናቸው። የጋራ ንቅናቄያችን ከተመሠረተበት ዓላማ አኳያ ለእነዚህ ውድ ዜጎች ህልውና መታገል አንዱ ሲሆን ሌሎች ኢትዮጵያውያንም የእነዚህን ወገኖቻችንን መከራና ስቃይ እንዲጋሩ በማድረግ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ አብሮ ሊከናወን የሚገባው ተግባር እንደሆነ ያምናል፡፡"ከጎሳ ይልቅ ሰብአዊነትን" ማስቀደምም ቀዳሚው ዓላማችን ነው፡፡

የቦዲ፣ የሙርሲ፣ የኮዌጎ፣ የሱሪ፣ የሃመር፣ የካሮ፣ የኒንጋቶም፣ የዳሶናች ወዘተና ሌሎች ኢትዮጵያውያን አንድ ነን!! ቀለማቸው ጥቁር ሆነ አልሆነ፣ እርቃናቸውን ሄዱ ልብስ ለበሱ፣ የተማሩ ሆኑ ያልተማሩ፣ የሰለጠኑ ሆነ ያልሰለጠኑ ወገኖቻችን ናቸው። ሰብአዊነትን ስናስቀድም የነሱ መጨቆን የኛም መጨቆን ነው። የነሱ ነጻ አለመሆን የእኛም እስር ነው።

ዘር በማጥፋትና ሰብአዊ መብቶችን በመጣስ የሚታወቀው ህወሃት/ኢህአዴግና የአቶ መለስ አገዛዝ በጋምቤላና ኦጋዴን እንደተፈፀመው አይነት የዘር ማጥፋት ተግባር በእነዚህ የኦሞ ህዝቦች ላይ ለመድገም ያሴረ ለመሆኑ ከሚያደርጋቸው ተግባራት ለመገመት ይቻላል፡፡ **በመሆኑም በያደባባዩ ምስላቸውና እዛው የጥንቱ ዘመን ላይ እንደተሰቀለ የቀረውን አኗኗራቸውን የሚያሳዩ ምስሎችን ለማስታወቂያነት በመጠቀም ለቱሪዝም ንግድ ግምባር የሆኑ ህዝቦችን መታደግና "እንደኔ ናቸው" ብሎ ማሰብ የወቅቱ ጥሪ ነው።** የድረሱልን ጥሪው የነዚህ ህዝቦች ነው ምላሹ ግን የእኛ መሆን አለበት፡፡ በብሄር ብሄረሰቦች ስም የሚገዘተው ህወሃት/ኢህአዴግ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወታደሮች አሰማርቶ መጠነ ሰፊ ጥቃት ለመሰንዘር አሰፍስፏል፡፡

በመሆኑም እነዚህ ህዝቦች የድረሱልን ጩኸት ለሁሉም ወገን እያሰሙ ነው። የችግሩ ሰለባ እንዲህ ይላሉ ". . .**በዓለም ሊረዳን የሚችል አካል አለ ወይ?...እባካችሁን በተፈጠርንበት ምድራችን እየደረሰብን ካለው መከራ ታደጉን። አሁኑኑ አድኑን!!**" የጋራ ንቅናቄያችንም ጥሪ ይኸው ነው!!

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

****

ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡